# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 ቿፍትሕ፣የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ሳምንታዊ ልሳን፤

www.ginbot7.org

ቁጥር 28 ሕዳር 18 2001 ዓ.ም

**አንብበው ያስነብቡ ! አባዝተው ያሰራጩ !**

***"”ህዝብ፣ የዴሞክራሲ መንፈስና ፍላጎቱን በኢኮኖሚ እድገት እንዲለውጥና ቀልቡን ከፖለቲካው ለማላቀቅ በሚል ስሌት ገደብ በሌለው የመንግስት ብድርና ብር ማተም ላይ የተመሰረተ ጊዜያዊ የኢኮኖሚ ሞቅታ እያደር በሰዎች የለት ተቀን ኑሮ ላይ የሚያመጣውን አስከፊ አበሳ እያየነው ነው።”***

**ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ከግንቦት7 ድምጽ ራዲዮ ጋዜጠኛ ጋር ያደረጉት ቃለ ምልልስ**

**(የቃለምልልሱን ክፍል አንድ በገጽ 3 ያንብቡ )**

## “የኢትዮጵያ “መንግስት” ወታደሮቹን ወደ ዳርፉር ሊያዘምት ነው” ጄንድል ፍሬዘር

በቢሲ ቴለቪዥን “ሃርድ ቶክ” በሚባለው ፕሮግራም ቃለመጠይቅ የተደረገላቸው የአሜሪካ መንግስት የአፍሪካ ጉዳይ ሃላፊ ወ/ሪት ጀንደል ፍሬዘር አሜሪካ በምስራቅ አፍሪካ ያለውን አለመረጋጋት ለመቋጨትና የአሜሪካንን ጥቅም ለማስጠበቅ የቡሽ አስተዳደር የሚከተለውን ፖሊሲ ከግብ ለማድረስ ከሚያደርጉት እንቅስቃሴ አንዱ የሆነውን በዳርፉር የሚደረገውን ግጭት ለመፍታት ከመለስ ዜናዊ አገዛዝ ጋረ እንደዚህ ቀደሙ ሁሉ ስምምነት ላይ መድረሳቸውን ገልጸዋል። ስምምነቱ...... **(ወደ ገጽ 4 የዞረ)**

## “በኢትዮጵያ የሴቶች መብት ረገጣ እጅጉን እየከፋ መጥቶአል” አለም አቀፍ ኢኮኖሚክ ፎረም

የመለስ አገዛዝ ስልጣን ላይ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የሴቶችን መብት እና ተሳትፎ ለመጨመር በሚል ስም የምእራባውያንን መንግስታት በማታለልና በሴት እህቶቻችን ስም የሚገኘውን የእርዳታ ገንዘብ ያለአግባብ ሲመዝ መቆየቱ የሚታውቅ ነው። ይሁን እንጂ ይህ ያረጀ የማጭበርበር ዘዴው ከምርጫ 1997ዓ.ም ጀምሮ በተለያዩ አጋጣሚዎች ለአለም ህዝብ እውነታው መጋልጥ በመጀመሩ አገዛዙን እያስደነገጠው መምጣቱን በተለያየ ጊዜ የሚዎስዳቸው የደመነፍስ እርምጃዎች አስረጂዎች ናቸው።ሰሞኑን መሰርቱን በጄኔቫ ያደረገው የአለም የኢኮኖሚክ ፎረም በመባል የሚታወቀው ድርጅት ኢትዮጵያ በ2007 በአውሮፓ አቆጣጠር ከነበራት ዝቅተኛ የሴቶች መብት አጠባበቅ ደረጃ (113ኛ) አሽቆልቁላ ዘንድሮ በ122 ደረጃ ላይ መሆኑዋን አስታውቆዋል። ድርጅቱ እንደ መለኪያ የተጠቀመባቸው አራት መሰረታዊ የሰውልጆችን መብት የሚያጠቃልሉ ነጥቦችን ሲሆን፤ እነሱም በኢኮኖሚ ላይ ያላቸው ተሳትፎ እና የተሰጣቸው እድል፤ በትምህርት ያላቸው ውጤታማ ተሳትፎ፤ በፖለቲካው ያላቸው ትሳትፎና በጤና መሆናቸው ተገልጾአል። ድርጅቱ በሪፖርቱ አገዛዙ ከሌሎች አገሮች ጋር ሲወዳደር ብቻ ሳይሆን ከራሳቸው የ2007 አመት የሴቶች መብት አከባበር ክንውን በእጅጉ ያሽቆለቆሉ መሆኑን ጨምሮ ገልጾአል። በተለይም ሴቶች በኢኮኖሚው መስክ እና በትምህርት ባላቸው ተሳትፎ ከሌሎች ሀገሮች እጅግ አሽቆልቁላ መገኘቷን ድርጅቱ ጨምሮ ገልጾአል።

አገዛዙ በሚከተለው የማስመሰል ጥበቡ ጥቂት ሴቶችን ለይስሙላ በምክር ቤት በመጨመር እና በሸራተን በሂልተንና በጊዎን ሆቴሎች ለሴቶች ጉዳይ በሚል ሰበብ በሚደረጉ የካድሬዎች ስብሰባ ያውም በአንድ ዝግጅት በሚሊዎኖች የሚቆጠሩ ብሮች ወጪ የሚደረግባቸው፤ ነገር ግን የአንዲት ገበሬ ሚስት ህይወት ያልተቀየረባቸው ውጤት አልባ ዝግጅቶች ማድረጉ ለአምባገነኑ መንግስት የዜና አውታሮች ወሬ ከማምረት በተጨማሪ የገንዘብ እርዳታ ከመሰብሰብና በለጋሽ መንግስታት ፊት የሴቶች መብት ተቆርቋሪ መስሎ ከመታየት ያለፈ አላማ ያዘሉ አለመሆናቸው ግልጽ ነው።

ከእዚህ ከሴቶች ጉዳይ ጋር በተያያዘ፤ በ 21ኛው ክፍለ ዘመን አገዛዙ የተለያዩ የድለላ ተቋማትን በማቋቃምና ሴት እህቶቻችንን ሀላፊነት በጎደለው መልኩ ለስራ በሚል ሽፋን ወደ አረብ አገር በመላክ ለዘመናዊ ባርነት ያጋለጣቸው መሆኑ ይታወቃል። በተለያየ ጊዜ በነዚህ እህቶቻችን ላይ የሚደርሰው ኢ-ሰብአዊ ጥቃት እየበዛ ከመምጣቱም በላይ በየጊዜው ወደ ሀገር ቤት የሚላኩት የቆሰሉ፤ ያበዱና ህይወታቸው በግፍ ያለፉ እህቶቻችን ቁጥር እጅግ እያሻቀበ መምጣቱን የተለያዩ መገናኛ ብዙሃን ዘግበዋል።

አንድ በሃገር ውስጥ ለሴቶች መብት የቆመ የግብረ ሰናይ ድርጅት ውስጥ የሚያገለግሉ ወጣት የሴት ጠበቃ ለዝግጅት ክፍላችን እንዳሉት ‹‹በሀገር ቤት በሴቶች እህቶቻችን ላይ ከሚደረስው ጭቆና ባሻገር በተለያዩ የዜና አውታሮች ላይ በሴት እህቶቻችን ላይ ስለሚደርሰው አሰቃቂ አደጋ መስማት እየተለመደ የመጣ አሳዛኝ ክስተት ሆኗል። በነዚህ ጉዳዮች ላይ አገዛዙ ድምጹን ለዓለም ህዝብ አለማሰማቱ ያስገረማቸውአለማቀፍ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች በስደት በአረብ አገር ላይ ያሉ ሴት እህቶቻችንን ጉዳይ ይዘው ሲታገሉ ማየት ብሄራዊ ውርደት የሚያጎናጽፈን ብቻ ሳይሆን መንግስት ምንያህል ለዜጎቹ ሀላፊነት የማይሰማው መሆኑን›› ያሳያል ብለዋል። ከዚህም በተጨማሪ አሁን በአገዛዙ ምክር ቤት ለማጽደቅ ያቀረበው የግብረሰናይ ድርጅቶችን ለማፍን የተዘጋጀው ረቂቅ ህግ ሊያጠፉቸው ከሚፈልጋቸው ድርጅቶች አንዱ በውጭ የገንዘብ እርዳታ የሚንቀሳቀሰውን የሴቶች ጠበቆች ድርጅትን መሆኑን ስንመለከት አገዛዙ ሴቶችን ከምእራባውያንና ከአረቦቹ ገንዘብ ከመነገጃነት የተሻለ ነገር አድርጎ እንደማያያቸው ያረጋግጣል። የኪራይ ሰብሳቢአመለካከት ይሏል ይህ ነው›› ብለዋል

## የወላጅ አልባ ህጻናት ቁጥር በከፍተኛ ደርጃ መጨመሩ ተገለጸ

በትናንትናው እለት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በኢትዮጵያ ያለው ችግር ትልቅ የሰብአዊ ቀውስ መሆኑን ባተተበት ሪፖርቱ እንደገለጸው ከ82 ሚሊዮን ህዝብ 6ሚሊዮን ወላጅ አልባ ህጻናት ናቸው ብሏል። ህጻናቱም በቁጥር አነስተኛ ከሆኑ አለም አቀፋዊ ድርጅቶች በስተቀር መሰረታዊ መንግስታዊ እርዳታ እንደማያገኙ፤ በተቃራኒው እንደዜጋ በከተሞች መንገዶች ላይ የመተኛት መብት እንኳን ተነፍገው ለአገዛዙ ፖሊሶች የደህንነት ሰዎችና ወታደሮች ኢሰብአዊ ድብደባ፣ እስራት እና ግድያ የተጋለጡ መሆናቸውን አስታውቋል። ይህ የወላጅ አልባ ህጻናት ቁጥር በሃገራችን ከሚገኙት ህጻናት ቁጥር ጋር ሲነጻጸር እጅግ የሚያስፈራ መሆኑን የገለጹ አንድ የግብረሰናይ ድርጅት መሪ የሆኑ ግለሰብ፤ እንዳብራሩት ይህ ቁጥር ከ80 ሚሊዮን ህዝብ ጋር ሲወዳደር

**(ወደ ገጽ 4 የዞረ)**

## ርእሰ አንቀጽ

# ወይ ነዶ ኢትዮጵያ! ማነው ተጠያቂው?

ስድስት ሚሊዮን ህጻናት፣ ከአምስቱ ህጻናት አንዳቸው አባትና እናት የሌላቸው የሙታን ልጆች፤ የተቀሩት ህጻናት ከሙታኑ ልጆች ልዩነት በሌለው የኑሮ መቃብር ከነወላጆቻቸው የሚኖሩበት ሃገር፤ ኢትዮጵያ።

አስራ አራት ሚሊዮን፣ ህዝብ ከስድስቱ ዜጋ አንዱ፣ በውጭ መንግስታት እርጥባን ስጋን ከነፍሱ አጣብቆ የሚያድርባት ሃገር፤ ኢትዮጵያ። ሶስት ሚሊዮን የሚሆን ህዝብ፣ ከሃያ አምስቱ ዜጋ አንዱ ከአስከፊው የኤድስ በሽታ ጋር የሚኖርበት፤ በየአመቱ በሚሊዮን የሚቆጠር በሳንባ ነቀርሳ በወባ፣ በተስቦና ከአለማችን በጠፉ በሽታዎች የሚያልቅበት ሃገር፤ ኢትዮጵያ!

ወገኖቻችን ለሀገራችን ህልውና መከበርና ለነጻነታችን መጠበቅ በታሪካቸው የከፈሉትን መስዋእትነት የሚመጥን ስልጣኔ አልተቀዳጀንም፤ ለአርነታቸው ያሳዩትን ቀናኢነት የሚያንጸባርቅ መብት አልተላበስንም በማለት‹‹ እምቢ ለጭሰኛነት እምቢ ለገባርነት›› ብለው በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ብሩህ አእምሮ የነበራቸው ወጣት ተማሪዎችና ምሁራን እንደቅጠል የረገፉበት፣ መስዋእትነታቸው ከንቱ ሆኖ፣ በመሳፍንቱና በባላባቱ ምትክ ጥቂት ዘረኛ ደናቁርት ተተክተው ሃገሬውን በሙሉ ገባር አድርገው የሚኖሩበት ሃገር፤ ኢትዮጵያ! ለሽዎች አመታት ነጻነቱን በከፍተኛ መስዋአትነት አስጠብቆ የኖረ ህዝብ ለጥቂት ዘረኞች ባርያ ሆኖ የሚኖርበት ሃገር፣ ኢትዮጵያ!

ስልጣን ከማእከሉ እጅ ወጥቶ ህዝብ ራሱን በራሱ ወደሚያስተዳደርበት መንደርና ቀበሌ ድረስ ይውረድ፣ ሁሉም ቋንቋውን ባህሉን የሚጠቀምበት የሚያሳድግበት እኩልነቱ ይከበር ለሚል ፍትሃዊ ጥያቄ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ወገኖቻችን አልቀው፣ ጥቂት ዘረኞች የሀገሪቱን የፖለቲካ ስልጣንና ምጣኔ ሃበት ተቆጣጥረው በታሪካችን አይተነው የማናውቀውን በዘር ላይ የተመሰረተ አስከፊ ዘረፋና መጠቃቀም የሚያካሂዱበት ሃገር፤ ኢትዮጵያ!

ትውልድ እየተፈራረቀ ልጆቹን ያለ አሳዳጊ ፣ወላጆቹን ያለጧሪ፣እየተወ፣ ያለስንቅና ያለበቂ ትጥቅ፣ በባዶ እግሩና በባዶ ሆዱ በደሙ ዋጅቶ አጥንቱን አድቅቆ አቡክቶ ያስጠበቀውን ዳር ድንበር የሚንድ ፈሪ የባንዳ ውላጅ በጀግኖቹ ዙፋን ላይ የወጣበት ሃገር፤ ኢትዮጵያ!

የራሷን አስደፍራ የሌላውን ደፍራ የማታውቅ ሃገር፣ ከአሜሪካንና ከእንግሊዝ መንግስታት ጋር የነበራቸውን ወዳጅነት ሰበብ ሳያደርጉ፣ ዘረኛውን የደቡብ አፍሪካ ይታገል የነበረውን ኔልሰን ማንዴላን በሚሰጥር የውጊየ ትምህርት ለመስጠት፣ በጥቂት የሮዴሽያ ነጮች ለሚረግጡት አፍሪካዊ ወገኖቻችን፣ በቅኝ ግዛት ሰንሰለት ተጠፍረው ለሚኖሩ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የአፍሪካ ሃገሮች የዲፕሎማሲና የትጥቅ ድጋፍ በማድረግ አኩሪ ታሪክ ያነበራቸው መሪዎች ታሪካቸው ፍትሃዊ ሚዛን አጥቶ በተቀበሩበት፤ ህዝብን እየረገጡ ስልጣን ላይ ለመቆየት በሚል ስሌት ለአሜሪካን እሽክርና አድረው የጎረቤት ሃገሮችን በመውረር በስማችን አሰቃቂ ወንጀል በጎረቤት ወንድሞቻችን ላይ የሚፈጽሙ፣ በሀገራችን ላይ በዙሪችን የሚገኙ ሃገሮች አይናቸው እንዲቀላ የሚያደርግ በደል የሚሰሩ ከሀዲዎች ስልጣን ያያዙበት ሃገር፤ ኢትዮጵያ!

‹‹ሂዱ እናንት ተከታዮቼ ወደ ኢትዮጵያ አቅኑ፣ በእዛ የሚገኘው ብጹእ የክርስቲያን ንጉስ ከክፋት ይጠብቃችኋል* በማለት ነብዩ መሃመድ ቤተሰቦቹንና የመጀመሪያ የእስልምና እምነት ተከታዮቹን ወደ ኢትዮጵያ በመላክ የባረካትን፣ ለረጅም ዘመን የክርስትናና የአስልምና እምነት ተከታዮች በሌሎች ቦታዎች ታይቶ በማይታወቅ መፋቀር በኖሩባት ሃገር ህዝብ በሃይማኖት እንዲናከስ፣ ሞቃዲሾ ውስጥ ቅዱስ መስጊድ ውስጥ ገብቶ ህጻናትና አረጋውያንን የሚያርድ፣ በደቡብ ኢትዮጵያ በቤተክርስቲያን መቅደስ ውስጥ ቀሳውስትንና ምእመናንን በቆንጨራ የሚያስጨፈጭፍ፣ ህዘብን በዘር ለማናከስ ከሚሰራው እኩይ ተግባር በተጨማሪ በሃይማኖት እንዲባላ የሰይጣን እንጀራ ለመጋገር ሴራ ሲያቦካ የሚያድር ገዥ የተቆለለባት ሃገር፤ ኢትዮጵያ!

ገንዘብ ያለው ዜጋ ገንዘቡን የሚያሸሽባት፣ እውቀት ያለው ዜጋ እውቀቱን ይዞ ከሃገር የሚፈረጥጥባት፣ ሙያ ያለው አክብረው ለሚያሰሩት ሌሎች ጌቶች ሙያን ለመሸጥ ሃገር ጥሎ የሚሮጥባት፣ ጉልበት፣ አቅሙ ቢኖረውም ዘዴውን ቢያውቅበትም ሁሉም ሃገሩን ለጥቂት በዘረፋ ተንደላቀው ለሚኖሩና በያዙት ጠመንጃ ያሻቸውን ፈጽመው ለሚያድሩ ዘረኞች ጥሎ ለመጥፋትና በአለም ላይ እንደ አሸዋ ለመበተን የተዘጋጀበት ሃገር፤ ኢትዮጵያ!

የመከራና የሰቆቃው ጥልቀት መዳበሻ ያጣ፣ የሲቃችን ፍጻሜ ጭላንጭሉ የማይታይበት ሃገር ኢትዮጵያ! እረ እንዴት ነው ነገሩ ይህች የሚገርም የሚያኮራ እንደ እንቁ የሚያበራ ታሪክ የሚያስደንቅ መልክአ-ምድር፣ የአየር ጠባይና የተፈጥሮ ሃብት ያላት ሃገር፣ በማንኛውም መመዘኛ ከሲኦል ልዩነት የሌለው ሕይወት የአብዛኛው ህዝቧ እጣ መሆን የቻለው? እንዴት ነው ዛሬ ካለንበት፣ ከውርደትም በአስከፊ ውርደት በተሞላ አሳፈሪ ሁኔታ ውስጥ መውደቅ የቻልነው? እውን ይህን የሃገራችን መከራና ስቃይ፣ በየግዜው ስልጣን ላይ በመጡ ገዥዎች እኩይነት ሙሉ በሙሉ አሳበን፣ ይህንን ሁሉ የሰሩት ያደረጉት እነሱ ብቻ ናቸው ብለን ተናግረን ህሊናችን በሰላም ማዋልና ማሳደር የቻለናልን? እውን ገዥዎቻችን ሃገራችንን እና ሁላችንንም እንዲያዋርዱን ሳንፈቅድላቸው ብቻቸውን ተነስተው ይህን የውርደት፣ ሃገር የማጥፋት የክህደት፣ የዘረኛነትና የዘራፊነት መርሃ ግብር ማስፈጸም ይችላሉ?

ስለሰው ልጆች ነጻነት ብዙ በሚያስተምረው የፍልሰፍና ትምህርት ዶክተር የሚል ማእረግ የተሰጠው የዩኒቨርሰቲ ፕሮፌሰር ራሱንና ተማሪዎቹን ለደንቆሮዎቹ የወያኔ ካድሬዎችና ሰላዮች በፍርሀት አስገዝቶ ለመኖር ሲቆርጥ አዋርዱኝ የሚል ፈቃድ ለአዋራጆቹ መስጠቱ አይደለምን? የከፍተኛ ተቋማት ተማሪዎችስ? ባገኙት እድል የቀድሞ ተማሪዎች መብተቻውን ከማስከበር፣ ዩኒቨርስቲያቸውን በነጻነት የመማሪያና የማስተማሪያ ቦታ ለማድርግ የከፈሉትን መስዋአትነት እያወቁ፣ ከእዛም በላይ እንደነሱ የእውቀት ብርሃን ለማግኘት ያልታደለውንና በሚከፍለው ግብር የሚየስተምራቸውን ደሃ ህዝብ መብት ለማስከበር ያደረጉትን የተጋድሎ ታሪክ እየሰሙ፣ ምንም አይነት ነጻነት በሌለበት፣ የትምህርት ደረጃው በወደቀ ዩኒቨርስቲ መማር፣ በመመረቂያ ወቅት፣ የስራ ወይም ከፍተኛ የውጭ የትምህርት እድል እንዲያገኙ ለወያኔ ኢህአዴግ ታማኝ ባሪያ ሆኖ ለማገልገል በፊርማቸው ሲያረጋግጡ መለስ ዜናዊን አዋርደን የሚል ፈቃድ አልሰጠነውም ማለት ይችላሉ? በዜግነቱ ማግኘት የሚገባቸውን መብት የወያኔ ካድሬዎችን ጫማ በመሳም፣ እኒህ የቀን ጅቦች በልተው የማይጠቅማቸውን ጉቦ በመስጠት የንግድና ኢንቨስትመንት ፈቃድ፣ የሃገር ውስጥ ብድር የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት የሚሞክረው ነጋዴ፣ የፋብሪካ ጌታ፣ የህንጻ ተቋራጭና ሌላውም ባለሃብት በሃገሩ ላይና በራሱ ላይ ለመጣው ውርደት ተጠያቂ አይደለሁም ይላል? በዜግነቱ ማግኘት የሚገባውን በሃገሩ የመኖር፣ ንብረትና ቤት የማበጀት መብት ለወያኔ አስረክቦ የወያኔን ችሮታ ለመቀበል በሃገሩና በወገኑ ላይ የሚደርሰውን ስቃይ ወደ ጎን ብሎ የመሬትና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን የሚያሳድደው በውጭ ሃገር የሚኖር ወገናችንስ ራሴን አላወረድኩም ለሃገሬ መዋረድ የድርሻዬን አለባረከትኩም ማለት ይችላል? የፖለቲካ ሰዎችስ? የፖለቲካ ድርጅት መሪዎችስ.? ከስሜ፣ ከግል ክብሬ፣ ከግልና ከድርጅቴ ጠባብ ጥቅም በላይ የሃገርና የወገን ጥቅም ይቅደም በሚል፣ ከሸፍጥ፣ ከክህደትና ከማንአለብኝነት መንፈስ ውጭ ተባብረውና ህዝብን አስተባብረው ለመነሳት ባለመቻላቸው የመለስ ዜናዊን ጸረ-ኢትዮጵያ አገዛዝ እድሜ አልቀጠልንም? በስሙ የምንምልለትን ህዝብ መከራ አላራዘምንም ማለት ይችላሉ? ማነው የማይጠየቅ? የመንግስት ሰራተኛው፣ ወታደሩ፣ የተቀረው ህዝብ፣ ቄሱም ሼኩም፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ለሚገኝበት እጅግ አሰቃቂ የሆነ የድህነት አዘቅት, የመብት እረጋጣ፣ የልኡኣለዊነት መገሰስ፣ መለስ ዜናዊ ሃገራችንን እየጋታት ላለው መርዘኛና ከፋፋይ የሆነ የዘርና የሃይማኖት ጭማቂ ተጠያቂ አይደለንም ማለት ይችላሉ?

ደረጃው ይለያይ እንጂ በሃገራችንና በራሳችን ላይ ለሚደርሰው ውርደትና ስቃይ ሁላችንም ተጠያቂዎች፤ ሁላችንም ወንጀለኞች ነን። ይህ ሃቅ ሽህ ግዜ ብንፍጨረጨር ፣ ምንም አይነት እራሳችንን የማጭበርብር ክህሎት ቢኖረን የማናመልጠው ሃቅ ነው። ይህንን በፍጥነት መረዳቱ የመከራ ቀናችን ለማሳጠር ትልቁ እርምጃ ነውና፣ ሁላችንም እራሳችን እንጠይቅ። እነዚህን በሃገራችን ላይ የነገሱ ጸረ-ኢትዮጰያና ጸረ ህዝብ ሃይሎች የሚፈጽሙትንና የሚያስፈጽሙትን ግፍና በደል ለማስቆም እያንዳንዳችን ራሳችንን ምን አድርጌአለሁ? ምን እያደረግሁ ነው? ብለን እንጠይቅ።

ግንቦት 7 ድምጽ በግንቦት 7 ለፍትህ ለነጻነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን

የፖስታ ሳጥን ቁጥር ፦ POBox: 4916
2003EX Haarlem
The Netherlands

# ከዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ

**ጥያቄ**: *በአጭሩ ግንቦት 7 አሁን አገራችን ያለችበትን የፖለቲካ ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ሁኔታ እንዴት ይመለከተዋል ?*

**ዶ/ር ብርሃኑ**: መቼም በአገራችን ያለው ሁኔታ ጥሩ ነገር የሚያመለክት ነው፤ አንዳንድ ነገሮች ችግር ላይ ያሉ ቢሆንም በአብዛኛው ወደ ጥሩ መስመር እየሔድን እንደሆነ እያየን ነው፡ ፖለቲካው የተበላሸ ቢሆንም ይህ ሀፍረተ ቢስ መንግስት እንደሚወተውተው ቢያንስ ኢኮኖሚው እየተሻሻለ፤ ሕዝቡም ‹በቀን ሶስት ጊዜ እየበላ ነው› የሚል አወንታዊ ነገር መናገር ብችል በጣም ደስ ባለኝ ነበር። በአገር ውስጥ የሚታየው ግን እያደር በጣም የሚዘገንን እየሆነ ነው። በአንድ ወቅት በዚህ ብካይ መንግስት ተጠቃሚ የሆኑ ግለሰቦች የራሳቸውን ጥቅም ከአገር ጥቅም ጋር በማሳከር፤ ሁኔታዎች ጥሩ ናቸው፤ ብዙ ፎቆች እየተሰሩ ነው፤ እድገት እየታየ ነው ይሉን ነበር። አሁን እነሱም ይህን ትተውታል። በአገር ውስጥ ስላለው ሁኔታ ከሁሉም አቅጣጫ የምንሰማው (ደግሞ በጣም በቅርብ ነው የምንከታተለው፤ ከመንግስት ተቃዋሚዎች ብቻ ሳይሆን ከመንግስት ባለሙዋሎችና ደጋፊዎችም እንሰማለን) በጣም አስከፊና የሚያስፈራ ነው። የሚገርመው ደግሞ በሁሉም አቅጣጫ ነው ነገሮች እየተላቀቁ የመጡት።

በፖለቲካው መስክ የነመለስ መንግስት ከዚህ በፊት ያደርጉት የነበረውን የማስመሰል ሙከራም ጭርሹንው ትተውታል። የአንድ ፓርቲ ለዘብተኛ አምባገነንነት ብቻ ሳይሆን በሶቭየት ጊዜ እንደነበረው የአንድ ፓርቲ ሁለንተናዊ አገዛዝ (totalitarian rule) ለማስፈን መወሰናቸውንና ይህንንም በግልፅ ለመናገር የደፈሩበት ሁኔታ ነው የምናየው። በተራ አምባገነንነትና በሁለንተናዊ አምባገነንነት መሀከል ያለው ልዩነት በቀላሉ የምናየው አይደለም። ከፊታችን የተደቀነውን አደጋ በቅጡ እንድንገነዘብ የሚረዳን ነው። እነመለስ ከስልጣን ለመውረድ አንፈልግም፤ ስለዚህም በጉልበት እንደገዛን እንቀጥላለን ማህበረሰቡ ስልጣናችንን ሳይነካብን ሌላውን ስራውንና ኑሮውን በእኩልነት ይቀጥል ብለው የሚተዉ እንዳልሆኑ በግልፅ ነግረውናል።

ለመነገድና ለማትረፍ የነሱ ፓርቲ አባል ወይም ግልፅ ደጋፊ፤ የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት የነሱ ተባባሪ፤ የተራብክ ገበሬ ከሆንክ የአለም ሕዝብ በስምህ የሰጠውን እርዳታ ለማግኘት ወይንም የማዳበሪያ ተጠቃሚ ለመሆን የነሱ ደጋፊ፤ የከፍተኛ ትምህርት ተማሪ ለመሆን ችሎታህ ሳይሆን የፓርቲ አባልነት ካርድ፤ ወታደር ሆነህ ለመሾም የተዋጊነትና የአዋጊነት ብቃትህ ሳይሆን ለነሱ ያለህ ፍፁም ታማኝነት፤ ከዚያም በተጨማሪ በመያድነትም ሆነ በባለሙያነት ለመደራጀትና ለመስራት በፓርቲውና በመንግስት ቁጥጥር ውስጥ ሆነህ እነሱ የሚሉህን ነገር ማድረግ እንጂ በነፃነት መንቀሳቀስ እንደማትችል በሚያወጡዋቸው ሕጎች፤ በድርጅታቸው የእስትራቴጂ ፅሁፎች፤ በእለት ተእለት ድርጊታቸው ግልፅ አድርገውታል። ስለዚህ የማጭበርበርና የማስመሰሉ ጊዜ አልቆአል። በአንድ ወቅት ስብሀት ነጋ ልክ ከምርጫ 97 በሁዋላ ያለውን ነገር በግልፅ ተግባራዊ ማድረግ ጀምረዋል። ‹ሕዝቡ በፈቃደኝነት በኢሕአዴግ ስር መኖር እንደማይፈልግ ካሳየ፤ ቢያንስ እንደ ደርግ በጉልበት ለሌላ 17 አመት መግዛት አያቅተንም› ነበር አለ የተባለው። ስለዚህ በነሱ አይን አሁን እዚያ እርከን ላይ ደርሰናል። በዚህ በኩል እኛ ፊት የተደቀነው ጥያቄ፤ በእርግጥ ሌላ 17 አመት ሊገዙን እንፈቅድላቸዋለን ወይንስ ታግለን በአጭር ጊዜ እንጥላቸዋለን? የሚለው ነው። ስለዚህ ከአሁን በሁዋላ የፖለቲካ ጨዋታው ያለው እነሱ ሜዳ ላይ ሳይሆን እኛ ምን እናደርጋለን የሚለው ላይ ነው። ስለእነሱ ፍላጎት ከአሁን በሁዋላ መወያየት ዝም ብሎ ጉንጭ ማልፋት ነው። እነሱ ወስነዋል። እኛም ወስነናል። ያልወሰነ ካለ ይወስን። ከአሁን በሁዋላ በምድሩ ላይ በተግባር የሚታየው ነው የመጨረሻውን ውጤት (የጊዜ ሰሌዳውን) የሚወስነው።

በኢኮኖሚው መስክ የሚታየው ሁኔታም እንደዚሁ እየለየለት ይመስላል። እያንዳንዱን ቀን እንዴት በስልጣን እቆያለሁ ከሚል ስሌት ብቻ ነገሮችን እያየ የሚንቀሳቀሰው የነመለስ የብልጥነት ጉዞ ጊዜያዊ ጥቅሙ ሲያበቃ ከበፊቱም እጅግ የባሰ ቀውስ እየፈጠረ እንደሚሄድ የመፅሀፍ ላይ ምሳሌ እየሆነ ነው የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ሁኔታ። የኢትዮጵያ ህዝብ በምርጫው ወቅት ያሳየውን የነፃነትና የዴሞክራሲ መንፈስና ፍላጎት በኢኮኖሚ እድገት እንዲለውጥና ቀልቡን ከፖለቲካው ለማላቀቅ በሚል ገደብ በሌለው የመንግስት ብድርና ብር ማተም ላይ የተመሰረተ ጊዜያዊ የኢኮኖሚ ሞቅታ እያደር በሰዎች የለት ተቀን ኑሮ ላይ የሚያመጣውን አስከፊ አበሳ እያየነው ነው። ለከት ከሌለው የብር አቅርቦት ጋር በቀጥታ የተገናኘው የዋጋ ግሽበት ሸማቹ ህዝብ ልጆቹን በተራ የሚያበላበት አስከፊና አዋራጅ ሁኔታ ውስጥ ከትቶታል። ሚሊየነር ሆነ የተባለው የኢትዮጵያ ገበሬ እንደወትሮው ትንሽ ዝናብ ሲጠፋ የሚራብ መናጢ ድሀ መሆኑን አይን አውጥተው ሊቀጥፉ ቢሞክሩም ሊደብቁት አልቻሉም። በዋጋ ግሽበት ምክንያት ለደጋፊዎቻቸው በነፃ ብቻ ሳይሆን ስለተበደሩ እየተከፈላቸው በተሰጣቸው ብድር የተሰሩት እነኛ ‹የእድገት አመልካች ህንፃዎች› በአጠቃላዩ የኢኮኖሚ ድቀተ ምክንያት የሚከራያቸው አጥተው በዶአቸውን እየተቀመጡ ሀላፊነት የጎደለው የሸፍቶች የኢኮኖሚ ፖሊሲ አሰቃቂ ውጤት ምልክት እየሆኑ ነው። ከዚሁ ጋር የተያያዘው በውሸት ብር ላይ የተመሰረተ ኢኮኖሚ የከፈተው የጥቂቶች የማይጠረቃ የፍጆታ ፍላጎት አገሪቱ ከምትችለው በላይ ከውጭ ስትገዛና በአንፃሩ ወደውጭ የምትልከው ምርት ማነስ የፈጠረው ክፍተት የአገሪቱን የውጭ ምንዛሪ ይዞታ እጅግ ከማሳነሱ የተነሳ የውጭ ምንዛሪ የነብስ አድን መድሀኒት ነው ቢባል በጣም ረጅም ሰልፍ ውስጥ ተገብቶና ለረጅም ወራት ጠብቆ፤ ያውም የመንግስት ባለሙዋሎች መልካም ፈቃድ ታክሎበትና፤ የየባንኩ ሙሰኞችና አቀባባይ ጉዳይ አስፈፃሚዎቻቸው ብዙ ጉቦ በልተውበት የሚገኝ ውድ እቃ ሆኖአል። በአጠቃላይ ኢኮኖሚው በአንድ ወቅት ለመግለጽ እንደሞከርኩት ጥቂት ዘራፊዎች ብዙሀኑን በማደህየት የሚጠቀሙበት የሸፍታ ካፒታሊዝም ሆኖአል። ጭራሹኑ ሳለመፍረስ የያዘው የውጭ የፖለቲካ ባለውለታዎቹ እርዳታ ብቻ ነው። በአለም ላይ የተፈጠረው የኢኮኖሚ ቀውስ ይህንን የእርዳታ ገንዘብ ያቀዘቀዘው ቀን (ይህ ደግሞ የሚቀር አይደለም) ከዚህም የባሰ መናጋት ውስጥ መውደቁን ለመተንበይ ጠንቁዋይ መቀለብ አያስፈልገውም።

በማህበራዊና በፍትህ ዙሪያ የምናየው ችግር እጅግ አስከፊ ባይሆን ኖሮ በጣም አስቂኝ ይሆን ነበር። በመጀመሪያ ይህ የዋጋ ንረትና አብሮት ያመጣው አስከፊ ድህነት እየፈጠረ ያለው ማህበራዊ ትርምስ በአጭር ጊዜ የማይለቅ ማህበራዊ እንደምታ ይኖረዋል። ከሰሞኑ የሰማነው የንግድ ስራ ኮሌጅ አንዳንድ ሴት ተማሪዎች ለምግብ ብለው ጊዜያዊ ሴተኛ አዳሪነት ሙያ ላይ መሰማራታቸው (ይህ እንግዲህ ከጋዜጠኞች ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ ፊት ለፊት የተነገረ ነው)፤ ሙስናው የደረሰበት ደረጃ ፊት ለፊት ቅሚያ ሊባል ምንም ያልቀረው መሆኑና ከሱ ጋር ተያይዞ የሚመጣው የማህበራዊ ሞራል መደርመስ፤ በመንግስት መሪነት የሚካሄደው ውሸትን ማእከል ያደረገ ማሕበራዊ ግንኙነት፤ ማሕበረሰቡ ያከብራቸዋል የሚባሉ ተቋዋማትን፤ ከተራ የሽምግልና ባህል እስከ ላቀው ሀይማኖታዊ ተቋዋማት ድረስ መንግስትን ለአንድ ተጨማሪ ቀን ስልጣን ላይ ማቆያነት እስከጠቀሙ ድረስ መጠቀሚያ ማድረግና ማዋረድ ምንም የማይጎረብጣቸው መሰሪዎች በስልጣን ላይ በቆዩበት እያንዳንዱ ቀናት በማህበረሰቡ ስነልቦናና የውስጥ እምነት ላይ የሚፈጥረው የረጅም ጊዜ ጠባሳ ጣጣው በቀላሉ የሚለቀን አይመስለኝም። ከነኝህ ሁሉ በተጨማሪና ከሁሉም በላይ ፍትሕ ስርአቱ ላይ እየተደረገ ያለው መሳለቅ ምንም ታሪካዊ ወደር የማይገኝለት ሆኖአል። እንደዚህ ወራዳ መንግስት ፍትህን የማጥቂያ መሳሪያ ያደረገ፤ ማህበረሰቡ ሕግና ፍትህ በሚባል ነገር ላይ ምንም እምነት እንዳይኖረው ሆን ብሎ የሚሰራና ይህንንም እንደ ትልቅ እውቀትና ብልጠት የሚቆጥር መሰሪ መንግስት ታይቶ የሚታወቅ አይመስለኝም። በጣም የሚገርመው ለመደበቅ እንኩዋን መሞከር እኮ ቀርቶአል። እኛ እነኚያ ቀጣፊና አሳፋሪ ዳኞች ፊት በምንቀርብበት ጊዜ በእውነት ነው የምልህ ይሰማኝ የነበረው የመቆሸሽ ስሜት እስከአሁን አልለቅ እንዳለ ጉድፍ ይሰማኛል። የኛን ጉዳይስ እሺ በቀጥታ በስልጣናቸው ስለመጣንባቸው ነው፤ ከስልጣን ሊነቀል ሲል የሚቅበዘበዝ እብድ ጭንቅላት የፈጠረው ጊዜያዊ መቃወስ ነው ብለን አይናችንን ጨፍነን እራሳችንን እንሸነግል እንበል። አሁን በዘፋኙ በቴዲ አፍሮ ላይ ፊት ለፊት በፍርድ ቤት የሚያደርጉትን ስትሰማ በእርግጥ ደምህን የሚያመር ነገር አለው። በጠራራ ፀሀይ የሞተ ሰውን የሞተበትን ቀን የሚያሳየውን ሰነድ ቀይሮ፤ በጊዜውና በቦታው ምንም ያልነበረን ሰው ሰነዱ የተሳሳተ ነው እንዲል አስመስክሮ፤ እሱ ራሱ ‹ፈርም ስለተባልኩ እንጂ እኔ አላውቅም ብሎ ሲመሰክር› ግድ የለም ብሎ ልጁን እስከአሁን በእስር ማንገላታት ዝም ብሎ የፍትህ መጉዋደል የምትለው ነገር አይደለም።

በአጠቃላይ ስርአቱ፤ እርከን ላይ የሚገኝ ሰው እንዲያምን ነው እየዘመቱ ያሉት። ዳኞቹ፤ በፖሊሱ፤ በአቃቤ ህጉ፤ እኛ ‹ሙያተኞች ነን ብለው በሚመፃደቁ ጠበቆች በሙሉና በአጠቃላይ ማህበረሰቡ ፍትሕ በሚባለው ነገር ላይ ያለውን እምነት ለአንዴና ለሁሌም ለማሳጣት የሚደረግ ጥልቅ ክፋት ሆኖ ነው ያገኘሁት። በዚህ ስርአት ላይ ለተከሳሽ መብት ጥብቅና ቆሜአለሁ ብሎ ከተከሳሽ ገንዘብ ተቀብሎ የሚበላ ሰው እንዴት ‹የድካሜን ዋጋ አገኘሁ› ብሎ ተስማምቶት እንደሚበላ በእውነቱ አላውቅም። እውነት የሚባል ነገር የለም፤ እውነት ማለት ጉልበት ነው ብሎ በሁሉም የሕብረተሰብ እርከን ላይ የሚገኝ ሰው እንዲያምን ነው እየዘመቱ ያሉት።

በሁሉም የሕይወት ዘርፍ፤ በትምህርት፤ በጤና፤ ሕብረተሰቡን እርስ በእርሱ በማናከስ፤ በዘረኛነት፤ ሰው አገሩን አማርሮ ጠልቶ እንዲሰደድ በመገፋፋት…ወዘተ. በፍፁም ለአገሪቱ እንጥፍጣፊ ስሜት እንኩዋን የሌላቸው መሰሪዎች አገሪቱን ገደል ለመክተት አስበውና አልመው የሚንቀሳቀሱ ነው የሚመስሉት። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

# የፖለቲካ ትንተና

በዚህ አምድ ስር ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ሌሎች ጉዳዮችን የሚመለከቱ መጣጥፎች ይቀርባሉ.

በውጭ ጉዳይም ላይ በሶማልያ የሚያደርጉትን ወራዳ ስራ ስትመለከት ለኢትዮጵያ ብዙ ዘላቂ ጠላቶች ለማፍራት የሚንቀሳቀሱ እንጂ የአገሪቱን ዘላቂ ጥቅም ለማስጠበቅ በሰፊው የታሰበበት እርምጃ እንዳልሆነ አሁን በቀላሉ ለማየት ይቻለናል። ችግሩ ዞሮ ዞሮ እነሱን መብላቱ አይቀርም እኔን የሚያሳስበኝ ለአገሪቱ ትተውት የሚሄዱት ዘላቂ ችግር ነው።

በአጠቃላይ በእኔ እምነት አገሪቱ በሁሉም መስክ በጣም መጥፎና እያደር እየተበላሸ የሚሄድ ሁኔታ ውስጥ እየገባች ነው። ይህንን በቶሎ ማስቀም ነው እንግዲህ ይህችን አገር እንወዳለን፤ ለዚህች አገር እናስባለን፤ ያለችን ይህችው አገር ነች፤ ለኛ እንኳዋን ባይሆን ለልጆቻችን የምትሆን አገር ትተን ማለፍ አለብን የሚል ኢትዮጵያዊን ሁሉ እንቅልፍ ሊነሳው የሚገባውና ከተራ ወሬ ተሻግሮ ተግባራዊ አስተዋፅኦ እንዴት ነው የማደርገው ብሎ በአስቸኳዩ እራሱን እንዲጠይቅ የሚያስገድደው።

***ጥያቄ : እነዚህን ምስቅልቅል ችግሮች ለመፍታት የመንግስት ለውጥ የማድረግ አስፈላጊነት ላይ ምንም ጥያቄ የሌላቸው እንዳንድ የህብረተሰባችን ክፍሎች በተለይ ከምርጫ 97 ቦኋላ የተከሰተው ዘግናኝ ሁኔታም ሆነ አሁን የሰፈነው ከፍተኛ አፈና ሳይበግረን በአገር ውስጥ ተደራጅቶ ቀደም ሲል ታድርጉት የነበረው ዓይነት ሰላማዊ ትግል ማድረግ ይቻላል ብለው ይከራከራሉ:: እርስዎ ይህንን እንዴት ይመለከቱታል?***

**ዶ/ር ብርሃኑ፤** ይህ ጥሩና መሰረታዊ ጥያቄ ነው። በእርግጥ ይህን እንቅስቃሴ ከጀመርን ጀምሮ ሲጠየቅ የነበረና አንዳንዱ ከልቡ በርግጥም ስላልገባው፤ አንዳንዱ የዚህ ጥያቄ ቀጥተኛ መልስ እንደ ሀይማኖት ከያዘው ቀኖና ጋር ስለሚጋጭበት ግራ በመጋባት ሌላው ደግሞ በህዝቡ ውስጥ መደናገርን ለመፍጠር ሆን ብሎ የሚጠይቀው ስለሆነ በተቻለ መጠን ምንም መደናገርን በማይፈጥር መንገድ መመለስ ወደፊት የምንሄድበትን መንገድ በማጥራት በኩል ከፍተኛ ጥቅም ስላለው በተቻለኝ መጠን በግልፅ ለመመለስ ልሞክር። እኛም የመረጥነውን የትግል አካሄድ ስንመርጥ እነኝህን ጉዳዮች አፅንኦት ሰጥተንና በሰፊው ጊዜ ወስደን ተወያይተን የደረስንበት ስለሆነ የአስተሳሰባችንን አካሄድ በዝርዝር ማቅረቡ ይጠቅማል የሚል እምነት አለኝ። ለዚህ እንዲጠቅመን በዚህ ጥቅል ጥያቄ ውስጥ የተሰገሰጉ ብዙ ጥያቄዎች ስላሉ በመጀመሪያ እነሱን በተራ እናስቀምጣቸው።

በመጀመሪያ እነኝህን ችግሮች ለመፍታት የዚህ መንግስት መውደቅ አስፈላጊ ነው ወይ የሚለው ጥያቄ አለ። በርግጥ በዚህ ጥያቄ ላይ ሁሉም ይስማማል ወይ የሚለው ጉዳይ ነው። ቢያንስ በተቀናቃኞች በኩል በግልፅ የዚህ መንግስት መውደቅ አስፈላጊ ነው በሚልና በአማራጭ የሚቀርበው ይህ መንግስት የችግሩ መፍትሄ አካል ሊሆን ይችላል፤ ስለዚህም ቀስ እያልን አብረነው እየሰራን ወይንም በሱ የጨዋታ ሕግ እየተጫወትን ወደ መፍትሄው በዝግታ ግን በእርግጥ መቅረብ እንችላለን የሚሉ አማራጮች ናቸው የሚቀርቡት።

ከዚህ ቀጥሎ የሚቀርበው ጥያቄ፤ እሺ በዚህ መንግስት መውደቅ ላይ ብንስማማ እንኳዋን የመውደቂያው መንገድ ምንድን ነው? በተለይ ደግሞ የሚወድቅም ከሆነ ብዙ ዋጋ ሳያስከፍል፤ ከወደቀ በሁዋላ የሚፈጠረው መንግስት ሌላ ችግር ውስጥ ሳይከተን ልንገላገል የምንችለው እንዴት ነው? የሚለው ጥያቄ ነው። በተለይም ደግሞ በአመፅ እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ስርአትን መፍጠር ይቻላል ወይ የሚለው ነው።

ከዚህ ጋር አብሮ የሚነሳው ጥያቄ የጊዜ ጉዳይ ነው። በምን የጊዜ ገደብ ነው የምናወራው? የሚለው ነው። መቼም ይህ መንግስት ዝም ብለን እንኳዋን ብንቀመጥ የስልጣን መዘውሩን የያዙት ሰዎች በተፈጥሮአዊ ችግር (ለምሳሌ እርጅና ወይንም በህመም) ቀስ ብለው መሞታቸው አይቀርም። ከነሱ በሁዋላና በነሱ ፈቃድ የሚመጡት የአዲሱ ትውልድ ገገርዎች ልጆቻችንን ከኛ ባነሰና ትንሽም በሰለጠነ መንገድ ሊገዙአቸው ይችሉ ይሆናል።ያ ከሆነ ደግሞ ‹ተቃዋሚ ነኝ› ብሎም መንቀሳቀስ፤ በዚያም ምክንያት መዋከብና ሌላውም እንዲዋከብ ምክንያት መሆን ሳያስፈልግ ዝም ብሎ የእግዚአብሄርን ታምር በመጠበቅ፤ ሁሉም የግል ኑሮውን እየኖረ፤ የሞተው እየሞተ፤ የተረፈው ተርፎ፤ አንድ ቀን ሊፈፀም ይችላል። ስለዚህ ከዚህ ጉዳይ ጋር አብሮ መመለስ ያለበት ሁላችንም በአእምሮአችን የያዝነው ከዚህ ብካይ ስርአት የምንገላገልበት የጊዜ ስሌት ምንድን ነው የሚለው ነው።

በመጨረሻም ተያይዞ የሚነሳው ጥያቄ የትኛው አካሄድ ነው በእርግጥ ውጤት የሚያመጣው አካሄድ? የትኛው መንገድ ነው በአጭር ጊዜ ወደ ውጤት የሚወስደን? የሚለው ነው። እንግዲህ እነኝህን አራት የተያያዙ ጥያቄዎች ነው በጥንቃቄና ግልፅ በሆነ መንገድ መመለስ የሚኖርብን።

የመጀመሪያውን ጥያቄ በሚመለከት እንደሚታወቀው እኔም በግሌ፤ ቅንጅትም ሆነ በምርጫ 97 ውድድር ውስጥ የተሳተፉት ድርጅቶች በሙሉ ያምኑበት የነበረው ኢትዮጵያን ወደ ዘላቂ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለመውሰድ በሚደረገው እንቅስቃሴ ከዚያ በፊት እነመለስ ሲወስዱዋቸው የነበሩት እርምጃዎች እንደተጠበቁ ሆነው፤ ኢሕአዴግም ሆነ በተለይ የሚያሽከረክሩት ዋና ዋና መሪዎች የጉልበቱ መንገድ እምብዛም እንደማያዋጣቸው ተረድተው፤ ወደ ልቡናቸው ተመልሰው፤ እያንገራገሩም ቢሆን፤ ቢያንስ ለታሪካቸው ሲሉ፤ የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታው አካል ይሆናሉ፤ በሕዝብ ድምፅ ቢሸነፉም ይቀበላሉ፤ አለያም ቢያንስ ወደዚያ መሸጋገሪያ የሚሆን የጥምር መንግስት ይቀበላሉ፤ የሚል እነሱ በሌላ መልኩ ያደረጉትን መሰል ‹የአደጋ ስሌት› (calculated risk) አድርገዋል። በዚህ ስሌት ገብተን፤ ከዚህ ውጪ ምንም ሌላ ዝግጅት ሳናስብ ምርጫ 97ና የተከተለው ጭፍጨፋ የተከሰተው።

አሁን የሚነሳው ጥያቄ ከምርጫ 97 የተማርነው ነገር አለ ወይ? (ይቀጥላል)

## የኢትዮጵያ... (ከገጽ 1 የዞረ)

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ሰራዊቱን ወደ ዳርፉር ለማዝመት በምትኩም የገንዘብና የወታደራዊ ድጎማ መስጠትን የሚያካትት ሲሆን ይህንንም ስምምነት በሃገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ የሚገኘው ኢትዮጵያዊ በገዛ ሃገሩ የመገናኛ ብዙሃን ወይም በፓርላማ ተብየው የእዚህ አስደንጋጭ ዜና ፍንጭ ባለመስማቱ በሴትየዋ ንግግር በጣም በመገረም ላይ መሆኑን የግንቦት 7 ድምጽ ለማወቅ ችሏል።

ይህን ጉዳይ በሚመለከት ያነጋገርናቸው አንድ የቀድሞ የአገዛዙ ዲፕሎማት እንደገለጹት ‹‹የወያኔ ቡድን ስልጣን ላይ ከወጣበት ሰአት ጀምሮ ከጊዜ ወደ ጊዜ ሊወጣው ወደ ማይችለው የፖለቲካና የኢኮኖሚ አዘቅት ውስጥ እየገባ ነው። ለዚህም በደመነፍስ በሚወስዳቸው እርምጃዎች ብዙዎችን ንጹሀን ዜጎች በመንገድ ላይ በአልሞ ተኳሽ ሲረፈርፍ፤ ብዙዎችን ሲያስር፤ ሲገርፍና እንዲሁም መሰረታዊ የሰብአዊ መብቶችን በመጣስ ላይ ይገኛል። ይህ አልበቃ ብሎት በሀገር ውስጥ እያደገበት የመጣውን ተቃውሞ ለመሸፋፈንና ከእንደ አሜሪካ ካሉ አገሮች ድጋፍ ለማግኘት ካለው አመለካከት በመነሳት የሀገርንና የህዝብን ብሄራዊ ጥቅም ወደጎን በመተውና ጎረቤት አገርን በመውረር ዜጎቻችንን በግፍ እያስጨፈጭፈ ነው። የሶማሌን ወረራ ብንመለከት መለስ ዜናዊ ጉዳዩን ለምክር ቤቱ ባቀረበበት ሰአት ወረራው ተጀምሮ የመከላከያ ሰራዊቱ በሶመሊያ ግዛት ውስጥ ገብቶ ነበር። በሶማሊያ ጉዳይ ላይ በምክር ቤቱ ወይይት በማድረግ ቲያትር እንዲሰራ የተደረገው መለስ ዜናዊ ፓርለማውን እሱ ሲያነፕስ መሃረብ ይዘው በሚቀርቡ ተላላኪዎቹ እንደሞላውና የፈለገውን ማስወሰን እንደሚችል ስላወቀው ነው። አሁንም በሱዳን የዳፉር ችግር ጣቱን ለማስገባት መለስ ዜናዊ ሲወስን ከአሜሪካ በላስልጣናት በስተቀር የገዛ የራሱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስተር የሚያውቀው አይመስለኝም። ይህ የሚያሳየው መለስ ዜናዊ የራሱ ካቢኔ ፓርለማ እና ሌሎችም ነገሮች የማይገድቡትና የማይቆጣጠሩት የለየለት አምባገነን መሆኑን ። በተለይ እንደ መለስ ዜናዊ አይነቱ ጸረ-ኢትዮጵያ አጀንዳ ያለው ግለሰብ እንዲህ አይነቱን ፍጹም ስልጣን ይዞ የሚከተላቸው የውጭ ፖሊሲዎች ሃገሪቱን በከፍተኛ ደረጃ የሚጎዱና በአካባቢው ካሉ ሃገሮች ጋር በማናቆር የዘመናት ቂመኛነት በሃገራችን የሚያተርፍ እንደሆነ ግልጽ ነው። ከሶማሊያ ውረደት ወደ ሱዳን ዳርፉር ለመግባት የሚያደርገው ህገወጥ ግስጋሴው የኢትዮጵያን መሰረታዊ ጥቅም ይጎዳል ከሚል ስሌት የሚከናወን መሆኑን የኢትዮጵያ ህዝብ ጥርጣሬ ሊኖረው አይገባም ብለዋል።

ዲፕሎማቱ አያይዘውም ‹‹ሀገሪቱ በዘመናት ታይቶ በማይታወቅ ረሀብና ሰብአዊ መብት ጥሰቶች በምትታወክበት፤አገዛዙ ህዝቡን በዘር፤በጎሳና በሀይማኖት ከፋፍሎ ለማፋጀት ድግሱን በሚደግስበት ወቅት እራሱ በዘር ማጥፋት ሊጠየቅ የሚችል ወንጀል በኦጋዴን፣ በኦጋዴንና በሌሎችም ብሄረሰቦች ላይ በፈጸመበት ሁኔታ በሌላ ሃገር ሰላም ለማስከበር የዘር ፍጅት ለማስቆም በሚል ሰበብ መንቀሳቀሱ አገዛዙ ይሉኝታ የሌለው አሳፋሪ ከመሆኑም በላይ አሜሪካ ይህንን የነፍስ ገዳዮች አገዛዝ በፈጸማቸው ወንጀሎች እንዲጠይቅ ከማድረግ ፋንታ የሰላም አስከባሪ በሚል ስም ወደ ዳርፉር ለማስገባት በምትከተለው የውጭ ፖሊሲ ልታፍር ይገባል። እርግጠኛ ነኝ ይህን የመሰለው አሳፋሪ ድርጊት ከቡሽ አስተዳደር ጋር የሚያከትም ይሆናል ብዬ አስባለሁ በማለት አስተያየታቸውን አጠናቀዋል።

## የወላጅ አልባ... (ከገጽ 1 የዞረ)

አጅግ የሚያስደነግጥ መሆኑን አውስተው ‹‹በሃገሪቱ ካሉት ከ4 ህጻናት መሃል አንዱ ህጻን ወላጆች የሌሉት መሆኑን ያሳየናል። ይህን እና በሃገሪቱ የሚገኙ ወላጆች ያላቸው ህጻናት የሚኖሩበትን አሰቃቂ ሁኔታ ደምረን ስንመለከተው ይህ የምንኖርበት ምድር ሃገር ሳይሆን ሲኦል የሚል ስም ሊሰጠው የሚገባ ቦታ ነው›› ብለዋል። ‹‹ይህን ሲኦል የፈጠርነውግን እኛ፣ የሚጠበበውም ነፍስ የእኛ፤ስይጣኖቹም ገዥዎቻችን ብቻ ሳይሆኑ ይህን አይነት ሃገር በእዚህ አሳፋሪ ሁኔታ እንዲገዙ የፈቀድንላቸው ሁላችንም ነን›› በማለት በምሬት አክለው ተናግረዋል።